ጸልዩ በአንድነት ለሰላመ ቤተ ክርስቲያን

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰሜን አሜሪካ የምዕራብ ስቴቶችና ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ማኅበረ - ካህናት

ቀን ነሐሴ ፲፫/፳፻ወ፬ ዓ.ም
ቁጥር ማ/ካ/002/2004

ጥልቅ የኃዘን መግለጫ

“ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር (መዝ ፻፲፭፥፮)”

ላለፉት ፳ ዓመታት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በፓትርያርክነት የመሩት
የብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክርቤት ኘሬዚዳንት
የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት እንደዚሁም የዓለም ሃይማኖቶች የሰላም አምባሳደር ዕረፍት ጥልቅ ኀዘን ተሰምቶናል።

ቅዱስነታቸው ባለፉት ፳ ዓመታት ለቤተ ክርስቲያናችን የሠሩት ቅዱስ ተግባር በቤተ ክርስቲያናችን መዝገበ ታሪክ በየግዜው የተመዘገበ ቢሆንም ለአዘክሮ ያህል፡

1. ቅዱስ አባታችን ቤተ ክርስቲያናችን በታሪክዋ አይታው የማታውቅ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ሀገር መንፈሳዊ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቷ የበለጠ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ከማድረጋቸውም በላይ **በዓለም አቀፍ ደረጃም ተሰሚነትዋ ብቻ ሳይሆን የመሪነት ብቃትዋ በቅዱስነታቸው ወሰን የሌለው ዕውቀትና ክህሎት ለማረጋገጥ ተችለዋል**፣
2. በዘመነ ፓትርያርክነታቸው 49 ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በመሾም የቤተ ክርስቲያኒትዋ አህጉረ ስብከቶች እንዲስፋፉ ከማድረጋቸውም በላይ በሀገር ቤትም በውጭም ባሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ዓብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ተርጓሚዎች እና አመስጣሪዎች ሊቃውንት እንዲመደቡ በማደርግ የቤተ ክርስቲያናችን የጀርባ አጥንት የሆነው ስብከተ ወንጌል በሁሉም አቅጣጫ እንዲስፋፋ እና እንዲጠናከር አድረገዋል።
3. በደረግ ተወርሰው የነበሩትየቤተ ክስርቲያናችን ንብረቶች ማለትም የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጨምሮ በብዙ ሚልዮንች ብር የሚገመቱ ሕንጻዎች እና ቪላ ቤቶች አስመልሰዋል።ተወርሶ የነበረው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በማስመለስ ፣ የመቀሌ ከሣቴ ብርሃን ማሰልጠኛ ት/ቤትም ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅ በማሳደግ እንደዚሁም የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ በከፈተኛ ደረጃ በማጠናከር፣ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ማዕከል እንዲሆን አድርጓል፣
4. ለዓብነት ትምህርት ቤቶች አስፈላጊውን በጀት በመመደብ እንዲጠናከሩ ከማድረጋቸውም በላይ በዘመናዊው ትምህርትም 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በየቤተ ክርስቲያኑ እንዲሠሩ መመርያ በመስጠት ብዙ ትምህርት ቤቶች ተሠርተው ለአገልግሎት እንዲበቁ አድርገዋል፣
5. በዘመናዊ ዲዛይኑ እና አሠራሩ የመጀመርያ የሆነው የጸርሐ መንበረ ፓትርያርክ ወቤተ መዘክር አሠርተዋል። እንደ ዓለም ዓቢያተ ክርስቲያናት መሪነታቸው ቤተ ክርስቲያናችን ዓለም ዓቀፍ ሃይማኖታዊ ጉባኤዎችን ማስተናገድ የምትችልበትን የተሟላ አገልግሎት መስጠት የሚችል አዳራሽና ጽ/ቤት አሠርተው ለአገልግሎት እንዲበቃ አድርገዋል።
6. ከቅዱስነታቸው ዘመነ ፓትርያርክነት በፊት ቅጥ ያልነበረው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ግቢ በማጽዳት ከሰባት በላይ የሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ህንጻዎች በማሠራት ቤተ ክርስቲያንትዋ የነበራትን በበረንዳ የመሥራት ልምድ አስቀርተዋል፣
7. የበይ ተመልካች የነበረው በሽዎች የሚቆጠር የቤተ ክርስቲያኒትዋ ሠራተኛ ደመወዝ በማሳደግና በማስተካከል በኑሮው እንዲለወጥ እና እንዲሻሻል አድርገዋል።

8. ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን በዘመነ ክህነታቸው እንደ ሐዋርያት ብዙ መከራ፣ ሥቃይ፣ መታሠርና መንገላላት የተቀበሉ ሰማዕት ሲሁኑ “ አባ ኅድግ ወሥረይ ሎሙ ኃጢአቶሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ ሉቃ ፳፫፥፴፬።የሚለውን አምላካዊ ቃል በተግባር ያሳዩ ቅዱስ አባት ነበሩ።
9. ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን በማህበራዊ ዘርፍም ችግሮኞችን መርዳት፣ የታመሙትን በየሆስቢታሉ እየተገኑ ማጽናናት፣ እስር ቤት ድረስ በመሄድ የታሰሩትን መጠየቅና ማጽናናት፣ የተጣሉትን ማስታረቅ የሚታወቁበት ልዩ ባሕርያቸው ነበረ ። በተለይም በዓለም ክርስቲያኖች ዘንድ ትልቅ ከበሬታና መወደድን ያተረፈላቸው በዓለም አብያተ ክርስቲያናት መከከል ሰላም እና አንድነት እንዲኖር የነበራቸው ከፍተኛ የመሪነትና የማስተባበር ቁርጠኛ አቋም ነው። በዚህም የሰላም አባት ተብለው ከአፍሪካ የመጀምርያ አፍሪካዊ ፓትርያርክ የሰላም ኖቤል ተሸላሚ ሲሆኑ “ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክርቤት ኘሬዚዳንት፣የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት፣ እንደዚሁም የዓለም ሃይማኖቶች የሰላም አምባሳደር” በመሆን በዓለማችን ሰላም እንዲሰፍን ደከመኝ ሰለቸን ሳይሉ ሠርተዋል፣

10. በመጨረሻም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ መሥዋዕተ ኦሪት የተሠዋባት፣ድህረ ልደተ ክርስቶስ በመሥዋዕተ ሐዲስ የከበረች የጽላተ ሙሴ መንበር በሆነቸው በርዕሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮን የሚገኙትን ንዋያተ ቅድሳትና ቅርሶች በዘመናዊ መልክ ተደራጅተው ለዕይታ የሚበቁበትን አንድ ታላቅ ታሪካዊ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ለማሠራት በማቀድ ፕላኑ በግሪኮችና በሮማውያን ባለሞያዎች እንዲጠና በማድረግ የግንባታው ሥራ አስጀምርው በማሠራት ላይ ሳሉ “ ኦ አዳም መሬት አንተ ወትገብዕ ውስተ መሬት” የሚለውን መለኮታዊ ቃል ደርሶ ያለ ጣርና ስቃይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተውናል። ለቅዱስነታቸው የጻድቃን ዕረፍት ቢሆንም ለቤተ ክርስቲያናችን ግን ትልቅ ኀዘን ነው።

ይሁን እንጂ በሠሩት ወርቃማ   ሥራ እየተጽናናን የጀመርቱን ውዝፍ የቤተ ክርስቲያኒትዋ ሥራ ከመፈጸም ወደ ኋላ አንልም።ዛሬ በሥጋ ቢለዩንም ቅዱስ መንፈሳቸው እና አባትነታቸው ከእነ ሕያው ሥራቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይደበዝዝ እና ሳይፋለስ ሲተላለፍ ይኖራል። በዚህ ቅዱስ ታግባራቸው ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር ታስባቸዋለች።

ከወራት በፊት ቅዱስነታቸው በካይሮ ደብረ ቢሾይ ገዳም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሥርዓተ ቅብር ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፣ ‹‹ሺኖዳ ከመላእክቱ ጋር ተቀምጠው ለኛ ይጸልዩልናል›› እንዳሉ እኛም ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ከመላእክት ጋር ሁነው ለቤተ ክርስቲያናቸን አንድነት እና ሰላም ወደ ፈጣሪያቸው ይጸልዩልናል። የቅዱስነታችው በረከት አይለየን እያልን ለሕዝበ ክርስቲያኑ እና ቤተ ሰባቸው መጽናናትን ለቅዱስነታቸው ዕረፍተ መንግሥተ ሰማያትን እንመኛለን።

የቅዱስ አባታችን በረከት አይለየን!!

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰሜን አሜሪካ የምዕራብ እስቴቶችና ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ሥር የምንገኝ
የአድባራት አስተዳዳሪዎች፣ካህናት፣ጸሐፊዎች፣ሰባኪያነ ወንጌል እና የሰንበት ት/ቤት ኃላፊዎች።